# “ኣውጣን!”







ዓለም በምን መንገድ ይጠፋ ይሆን፣
ማን ነውስ የሚያመልጥ፣ ማነው የሚድን?

በምን ዓይነት ይሆን የሰው ልጅ ፍጻሜ
ተቃርቧል እንግዴህ፣ ምንም የለው ዕድሜ

እንደ ሰዶም ሰዎች በእሳት ኣሎሎ
ይጠፋ ይሆን ወይ ተቃጥሎ፣ ተቃጥሎ…

ወይ በገዛ ራሱ ካመጣው ቆሻሻ
በዓዘቅት ተውጦ፣ ላያገኝ መድረሻ

ወይ የጥፋት ውሃ ኣጥቦ፣ ኣጥለቅልቆት
ያበቃለት ይሆን፣ እስትንፋሹ ጨንቆት?

ወይ ድድቅ በረዶ፣ ኣኮማትሮት ቆፈን
ኣልብሶ፣ ሽፍኖት፣ በጨለማ ይደፈን?

የቱ ይሻለው ይሆን መምረጥ ቢችል ሰው፣
ፍጡር መጥፊያውን መቸም ኣያውቀው

መዓቱም ዓይነቱ፣ ዕለቱ፣ ሰዓቱ
ተጽፎ ተይዟል ይብላኝስ ለእናቱ!

የማይቀር ዕዳ ነው፣ ብናውቅም፣ ባናውቅም
“ኣውጣን!” ማለት ደጉ፣ እኔ ኣልጨነቅም!

ገ/ኢ. ጐርፉ።